# <u>የሚቀጥለውን ምርጫ በኛ ቀመር የኛ ያሸናፊነት ውጤት እንዴት እናደርገዋለን?</u>

በዚህ አለም እስከኖርን ድረስ ማንኛውም ስህተት፣ መዘናጋት፣ ከጊዜ ጋር ማድረግ የሚገባን አለማድረግ፣ ሌላ የተሻለ መንገድስ የኖራል ብሎ አማራጮችን አለማየት....... ዋጋ ያስከፍላል። የምንራመድበትን መንገድ አጢነን እያየን ከአለመሄድ ተደናፍቀን በራሳችን ላይ ከምናመጣው ጉዳት ጅምሮ። የቤት ክራያችንን ተዘናግተን በሰአቱ ሳንከፍል ቀርተን ከምንከፍለው መቀጮ ወይም መኪና እየነዳን ሀሳባችንን መሪው ላይ ለትንሽ ደቂቃ ሳናደርግ ቀርተን በኛም ቤሌሎች ላይም የምናስከትለው አደጋ እያለ ይቀጥላል።

ይህ ጉዳይ በአገርና በህዝብ ላይ ሲሆን ጉዳቱ የከፋ ነው። ይህንን ከኛ በላይ የሚያውቅ መኖር መቼም የለበትም። አገራችንን ከዚህ በላይ ስህተት፣ ከዚህ በላይ መዘናጋትን፣ ከዚህ በላይ ያሉ አማራጮችን ሳይታዩ እንዲያልፉ ወይ ጊዜ የፈጠራቸውን አጋጣሚዎች ሳንጠቀም እንድናሳልፍ..... ሆና አይደለም ያለችን።

ከዚህ በኋላ ትክክል ለመሆን ያለ መስማማትን ወስደን። ውጤታችን ትክክል ያልነውን ከማሳካት ጋር ብቻ የሚለካ ብቻ እንደሆነ እናውቃለን። ትክክል፣ መደረግ ያለበት ነው ያልነውን  ሀሳብ አሸናፊ ተፈጻሚ ማድረግ ከአልተቻለም ጥፋቱ ከመነሻውም ስህተት የመሆን ያክል ነው። በአገራችን የጊዜው ሁኔታ እውነትን ትክክል የሆነውን መያዙ ብቻ ዋጋ ቢስ ነው ለማለት ነው። እንዲሁም ስህተት ከተሰራ በኋላ መደረግ ነበረበት ቢሆን ኖሮ አልጠቀመንም ። ይህ ለወደፊቱ በተወሰነ ደረጃ መማርያ እንጂ ያለፈ ሞቷል። በተወሰነ ደረጃ ያልነው ትናንት ትክክል ለማሰብ ትክክል ለመወሰን አጋጣሚን ለመጠቀም የነበሩ ሁኔታዋች ዛሬ ውስጥ ሁሉም የሉም። ዛሬ አዲስ ነው። ዛሬ ትክክል ለመሆን መቅረብ ከአለበት ልንመረምረው ከሚገባ ብዙ አማራጭ ሀሳቦች እንደአንድ ተደርጎ እቅዳችን ይወሰድልን።.

የቅንጅት መሪዎች ተፈተው በአሜሪካ ለስራ ጉዳይ በየከተማው ሲዘዋወሩ ተጣልተንበትም ቢሆን በአካል ለማወቅ፣ ልናስተናግዳት እደለኞች ለሆነው። ዛሬም ድረስ አፍሣው የሄደችው ፍቅሯ ከበሬታዋ ጥልቅ የሆነ አመለካከቷ ትናንትና ከኛ ጋር እንደነበረች ሆኖ የሚሰማን። ምርጫ የደረገችው ሰላማዊ ትግል ላይ በተደጋጋሚ ሞግተናት ከብረት የጠነከረ እምነቷንና ቁርጠኛነቷን ተግባራዊ እንደምታደርገው እርግጠኛነቷን ምስክር ልናደርገላት ለምንችለው። ስለዚህ እምነቷ ዋጋ እየከፈለችበት ላለችው ለወ/ሪ ብርቱካን ሜዴቅሳ  ክብር ይሁንልን።

<u>የሚቀጥለውን ምርጫ እስከ መሰናክሎቹ እኛን በሚጠቅም መንገድ ለመጠቀም መደረግ አለበት ያልነውን የኛን ሀሳብ ስናቀርብ አንባቢ ከዚህ በታች ያስቀመጥናቸውን ታሳቢ አድርጎ ያንብበን።</u>

1.ይህ የመፍትሄ ሀሳብ በጃችን በአለ ልናደርገው በምንችለው በኛ በኢትዮጵያዊያን አቅም፣ እውቀት፣ ችሎታ፣ ችግሩን መረዳት ላይ ብቻ ተንተርሶ የተሰራ ነው። እርግጠኛ የማንሆንበትን ከሌሎች አገሮች ህዝቦች ልናገኝ የምንችለውን እርዳታ ግምት ውስጥ ያላስገባ ነው። ብዙ እኛን የሚጠቅሙ የተሰሩ፣ ጊዜ የፈጠራቸው አጋጣሚዎች፣ ውጫዊ ሁኔታዎች እንዳሉ ግን እናውቃለን።

2.ስለሚቀጥለው ምርጫ  ይህ ቢደርግ ለማለት ሲታሰብ አሁን በአለው ሁኔታ ስለምርጫው ጠቅላላ ሁኔታ  ስለተሳታፊዎች አሰላለፍ የተወሰነ ነገር ማለት አግባብ ያለው ነው። ጀምረነው ነበር። አቶ ሽባባው ከአውሮፓ ይህንን አስመልክቶ እኛ ልንል ከምንችለው በላይ በሚገባ ጥርት በአለ ሁኔታ ስላጻፉበት እንዳለ ተቀብለንዋል። የመጨረሻ ይሆናል እስካሉት ትንቢታዊ ውጤት ድረስ። ለአንባቢ ድግግሞሽ እንዳይሆን በአጋዥ ዶክመንትነት ይያዝልን። የግድ ሊነበብ የሚገባው ነው። ለማንበብ ይህን ሊንክ ይጎብኙ።

http://www.ethiomedia.com/adroit/ethiopian_election.pdf

የዚህ ጽሁፍ አላማ ግን ችግሩን ከአወቅን የመጨረሻ ውጤቱን ላይ ስምምነት ከአለን ውጤቱን እኛን በሚጠቅም አሸናፊ በሚያደርገን መንገድ ልንቀይረው የምንችለው እንዴት ነው የሚለው ላይ ትንሽ ነገር ሞክረን በአለ እውቀቶችን ለተሻለ እቅድ እንዲሰሩበት ለማነሳሳት ነው።

3.ጽሁፉ መፍትሄ ለመጠቆም ሲባል ያሉ አመለካከቶችን የተድረጉ ውሳኔዎችን … በተወሰነ ደረጃ ሊቃወም ይችላል። ምንም አይነት ያለ አመለካከትን ለማጣጣል፣ ግለሰብንም ቡድንንም ለመቃረን ተደርጎ ግን አይወሰድ። በአንጽሮት ለመግለጽ በአጨሩ ሌላ መንገድ ስላጣንለት ነው።

4.በእምነት ደረጃ ወያኔን ለመጣል ሁለገብ ትግል ነው መደረግ ያለበት ብለን ነው የምናምነው። ከዚህም እምነታችን እኛ አገርቤት የሚደረገውን ጥረትም ምርጫውንም እንደትግል ነው የምናየው። አቶ ሽባባውም በጽሁፋቸው እንዳስቀመጡት በአራተኛ አገር አቀፋዊ ምርጫ ውሳኔያቸውን በግልጽ ለአሁኑ በአይገልጹም ምርጫው ውስጥ ተቃዋሚዎች መግባታቸው አይቀርም። <u>አንካፈልም ከሚለው ውሳኔያቸው ወይ ተካፍለው ምርጫውን የ97ቱን አይነት ከአላደረጉት በሁለቱም ወያኔ ተጠቃሚ ሆኖ የወጣል ብለን ፍራቻ አለን። ይካፈሉ አይካፈሉ የሚለውን አስበንበት ምርጫ ላይ መካፈሉ ግን ውጤቱ በኛ ስራና እቅድ …ላይ ስለሚወሰን እስከመሰናክሎቹ ምርጫው ላይ ቢካፈሉ ነው የሚሻለው የሚለው ሀሳብ ለኛ አሸንፏል።</u>

5.ለኛ ብዙም ጉዳቱ በአይታየንም እቅድ እነደመሆኑ ዝርዝር ሁኔታ ውስጥ ይገባል ሚስጥራዊነት ላይ ጥያቄ ያስነሳ ይሆን ብለን አስበናል። ስለዚህም መግቢያችንና እቅዱ ውጤታማ እንዲሆን መስተካከል ያለባቸው አመለካከቶች ላይ ከእቅዱ ጽሁፍ ውሳኔ፣ መተባበር፣ የወያኔ የምርጫ ዝግጅትና ምርጫውን ሊያካሂድበት የሚፈልገውን ብለሀት ላይ ብቻ ሀሳባችንን ሰተን ክፍል አንድ ጽሁፋችን ያቆማል። ህዝብ ውስጥ ገብቶ ከምናገኘው አስተያየትና ትግል ላይ ያሉ ድርጅቶች ስለጉዳዩ ከሚኖራቸው አመለካከት ጋር የቀረውን ዋና ዝርዝር እናስከትላለን።

# <u>ብርቱካን</u>

ብርትኳን ጣፍጭ ፍሬ። ለታመመ መጠየቂያ፣ ለታስረ ማጽናኛ ብርቱካን ለኛ ድሮም ቢሆን ለፈውስ ነው። ምርጫውን ብርቱካናዊ ለማድረግ ማን ከልክሎን። ብርቱካናዊ ምርጫ ብለን ጠርተነው ብርቱካናዊ ማድረግ እንችላለን።

## <u>እንደገና ልንመረምራቸው የሚገቡ የተሳሳቱ አዳካሚ አስተሳሰቦች</u>

ህዝብም ተቃዋሚዎችም ላይ የተሳሳተ በሚቀጥለው ምርጭ አዳካሚ ሊሆን የሚችል አስተሳሰቦች አሉ። እነዚህ አስተሳሰቦች ከምርጫ 97 በኋላ እነመለስ ከወሰዱት ዘግናኝ አፈና ጋር የተያያዙ ናቸው። ብርቱካናዊ ምርጫ ውጤት እንዲያመጣ እነዚህ አስተሳሰቦች ሊጠሩ ይገባል። አፈናው እነዚህን አደገኛ የተሳሳቱ አመለካከቶችን በህዝቡም በተቃዋሚዎችም ላይ በተወሰነ ደረጃ እንዲኖሩ አድርጓል። በተቃዋሚዎች በኩል የጥፋተኝነት የበዛ የሀላፊነት ስሜት። በህዝብ ዘንድ ተቃዋሚዎች የነበረቸውን አቅም በአላገናዘበ የትናንት ታሪክ ቢሆንም ነገሮችን አጣሞ ወያኔ ስልጣን ላይ

አሁንም ያለው በተቃዋሚዎች ስህተት አድርጎ ማየት። ምርጫን በሰለጠነው አለም ከሚጠቀሙበት መንገድ፣ ሊሰጠው ከሚችል ትርጓሜ ብቻ ተነስቶ ምርጫ አያስፈልግም በምርጫ ለውጥ አይመጣም፣ ድምጽ መስጠቱ ኮሮጆ ስለሚገለበጥ ዋጋ የለውም የሚል ምርጫ ላይ ያለ አስተሳሰብ። ወያኔ የወሰደው እርምጃ ወንጀል መሆኑ ቀርቶ ጥንካሬ ተደርጎ የመውሰድን ለለውጥ የነበርውን መነሳሳት እነመለስ የወሰዱት የሀይል እርምጃ ነው ያቆመው ብሎ ማሰብ ናቸው።

<u>በሰላማዊ መንገድ እየታገሉ ያሉ ተቃዋሚዎችን የበዛ አጥፊዎች ማድረግና፣ ይህ የፈጠረው ተቃዋሚዎች ላይ ላደመጠው የሚታይ የበዛ የሀላፊነት የጥፋተኝነት ስሜት</u>

ተቃዋሚዎች ዛሬም ድረስ ያ ሁኔታ እንዳይፈጠር ከነሱ በኩል ሊያደርጉት ይችሉ የነበሩትን ነገር ይመረምራሉ። ለሌላ መቶ አመት ሲብሰለሰሉበት ቢቆዩም ያኔ ከወሰዱት ትክክለኛ እርምጃ የተሻለ ነገር ማድረግ መወሰን አይችሉም ነበር። የነዛን ንጹሬን ዜጎች ሂወት ሊያተርፉ የሚችሉት እስከጭራሹ ለምርጫ በአይወዳደሩና በአያሸንፉ ነበር። ዛሬም እነዛን በግፍ ይተገደሉ ንጹሀን ከሞት አንስታችሁ ብትጠይቋቸው በሰላማዊ መንገድ ለምርጫ ተወዳድራችሁ ለምን አሸነፋችሁ አይሏችሁም። እነሱም መሰዋት ሲሆኑ ምክንያቱን አምነውበት ነው። መሰዋትነታቸው ለዘላለሙም አግባብ ላለው ለትክክለኛ ነገር የተከፈለ መሰዋትነት ሆኖም ይኖራል።

ህዝብም ውስጥ መነሳሳቱን ለማፈን ወያኔ ከወሰደው ከተጠና ከተቀናበረ የበዛ ዘግንኝ እርምጃ አኳያ ፣ ቅንጅት ምን ማድረግ ይችል ነበር? ምንስ አቅም ነበረው? የሚለውን ጠይቆ መልስ ከአለመስጠት እንዲሁ ለምክንያታዊነትም፣ ለፖለቲከል ጠቀሜታም ተብሎ የተደረገው መሪዎቹን ጥፋተኛ ስህተተኛ የማድረግ ስራ ህዝብ ውስጥ ሰርጾ በተወሰነ ደረጃ ውጤቱ እየታየ ነው። ወያኔዎች ደግሞ በጣም ሰርተውበታል እነመለስ ከምርጫ በኋላ ሰሩ ሊባልላቸው የሚችለው ትልቅ ስራ ይህ ነው። እኛም ከሚገባው በላይ አግዘናቸዋል ውጤታማ እንዲሆኑ ረድተናል። ይህ አደገኛ አስተሳሰብ ነው ተቃዋሚዎች በሚቀጥለው ምርጫ የሚኖራቸው ስኬት በተወሰነ ደረጀ ይህን አመለካከት እነሱም ለራሳቸው ከማሸነፍ ህዝብ ውስጥም ተቀባይነት እንዳይኖረው ለማድረግ ከሚሰሩት ስራ ጋር ይያዛል።

ይህ አመለካከት እንዲሰርጽ ሌሎች አገራትም አስተዋጾ አድርገዋል አሜሪካኖች መርጃ ድርጅታቸውም በርትቶ ሰርቷል። ይህን ለማወቅ ምንም የጠለቀ እውቀት አያስፈልግም ምርጫውን ከታዘበው የካርተር ማእከል ከሰጠው ግምገማ ጀምራችሁ እስቴት ዲፓርትመንት ያወጣቸውን ሪፖርቶች፣ ጽሁፎች፣ የህዝብ ተወካዮቻቸው የጻፏቸውን ደብዳቤዎች ሚዲያዎቻቸው ስለሁኔታው ያቀረቧቸውን ዘገባዎች ማጻመጥ መመርመር ብቻ ነው የሚያስፈልገው።

እነመለስ በምርጫ ተሸንፈዋል ኮሮጆ ገልብጠው ነው ስልጣን ላይ ያሉት ብለው በግልጽ አስቀምጠው አያውቁም። መረጃው እያላቸው ከምርጫው በኋላ ለተፈጁት ንጹሀን ተጠያቂው መለስ ነው በግልጽ አይሉም። ምንም ጥፋት እንደሌለባቸውም ቢያውቁም የቅንጅት መሪዎች ንጹህን ናቸው ብለው በግልጽ አስቀምጠውም አያውቁም። መለስ ኮሮጆ ገልብጠህም ለሚቀጥለው ምርጫ እነዚህን ጉዳዮች ለማስተካከል ቃል ግባና ግዛ ተብሎ እድል ተሰቶት እንደነበር በፍጹም አንዴም ተሳስተው እንኳ ገልጸው አያውቁም። ሌሎችን ብዙ ምክንያቶች መጥቀስ ይቻላል። ለምን ለሚለው? የኛን ችግር እነሱን በሚጠቅም ሁኔታ መጠቀም ይፈልጉ ስለነበር ነው። ተጠቅመዋልም ሰርቷልም ። ለጊዜው አንባቢ እንዲወስድልን የምንፈልገው የትናንት ታሪክ ሆኖ ይህ ተቃዋሚዎችን ስህተተኛ የማድረግ እነሱ ስህተት ስለሰሩ ነው ወያኔ ስልጣን ላይ ያለው የሚለው አስተሳሰብ ከየት የመጣ ነው ብላችሁ ብትጠይቁ አንዱ ምንጩ ይህ መሆኑ እንዲታወቅ ነው።

ሌላው ለወያኔ ዛሬም ስልጣን ላይ መኖር ከምርጫው በኋላ በይበልጥም ከተፈቱ በኋላ ቅንጅት መከፋፈሉ ነው የሚለው ሀሳብ ነው። ይህ ሀሳብ አንድ ከራሳቸው ከወያኔዎች ተደጋግሞ የሚነገር

ሲሆን ሁለት የተወሰነ እውነታን ይዘው ለፖለቲካል ፍጆታ ብቻ ሌሎች ፖለቲከኞቻችን የሚያነሱት ነው። መከፋፈላቸው ተቃዋሚውን ክፍል አዳክሟል አዎ፤ መከፋፈላቸው ለህዝቡ ጥሩ መልክት አላስተላለፈም እውነት። በአይከፋፈሉ ዛሬ ወያኔ አይኖርም ትግሉ የተዳከመው ስለተከፋፈሉ ነው ውሸት ። የተከፋፈሉት ከሁለት አመት በኋላ ከስር ሲወጡ ነው። ያኔ ትግሉ በተከታይ ተቀብሎ የሚመራው ቶሎ ሳያገኝ ቀርቶ በሌሎች ብዙ ምክንያቶች ተዳክሟል። በአይከፋፈሉ ጠንካራ ተቃዋሚ ዛሬ ለመፍጠር የሚደረገውን ጥረት ያስቀር ነበር እንጂ ወያኔን ለመጣል የሚያስችል አቅም ሁኔታዎች አልነበሩም። ወያኔ ስልጣን ላይ ያለው በቅንጅቶች ስህተት ነው ሲባል በጊዜ የሆነውን የተደረገውን በአለማጤን ወይ ሆን ተብሎ ከአልሆነ ይህ ሀሳብ ሲሰነዘር ቅንጅቶች በጊዜው ከነበራቸው አቅም በላይ በፍጹም ሊሸከሙት የማይችሉት የዱላ ውርጂብኝ ወያኔ እንዳወረደባቸው ግምት ውስጥ አያገባም። የህዝብ ለትግል መነሳሳቱ በነበረ ጊዜ መሪዎቹ በሙሉ ተሰብስበው እስር ቤት እንደነበሩ ይረሳል። ያልታሰሩትስ ምን አስቸጋሪ ፈታኝ ሁኔታ ውስጥ ነበሩ አይታይም። ይህ ማለት ስህተት አልነበረም ማለት አይደለም ወቀሳው በአግባብ አጥፊውን የሚኮንን አልሆነም። ከሚገባው በላይ ለሰበብነት የሚጠቀምበት ክፍል እየበዛ ስለሄደ ነው። ትግሉ ውስጥ እንዳለው እንዳብዛኛው እኛም በተመሳሳይ መነጽር ነው የምናየው። ወያኔ ስልጣን ላይ ዛሬ ያለው ከሚገባው በላይ የተቀናበረ አፈና ግድያ በገፍ እስር ብዙ አገርና ህዝብን አደጋ ላይ የሚጥል ውሳኔዎችን እርምጃዎችን አድርጎ ነው።

ከላይ ያስቀመጥናቸው የተሳሳቱ አስተሳሰቦች ተቃዋሚዎች ወደፊት በሚያደርጉት ትግል ላይ ተጽኖቸው ከአሁኑ እየታየ ነው። በጣም የበዛ የሀላፊነት ስሜትና፤ ተደጋግሞ ስለተባለ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ያለ ላዳመጠው የሚሰማ የጥፋተኝነት ስሜት አለባቸው። በሚቀጥለው ምርጫ ተወዳድረው ማሸነፍ ከፈለጉ ከዚህ የአይምሮ ሁኔታ ውስጥ መውጣት አለባቸው። <u>እነደኛ እንደኛ የመከዳት ስሜት በአይሰማቸው ይገርመናል። በግል የድርሻቸውን የተወጡ ጥቂቶች በአገርቤትም በውጪም ይኖራሉ እንደ አንድ አገር ህዝብ ግን ማድረግ የሚገባንን ያህል አላደረግንም ከድተናቸዋል።</u>

የምትገጠሙት በአላንጣ አስቸጋሪ እንደሆነ እናውቃለን። በሚቀጥለው ምርጫ ስትካፈሉ በተወሰነ ደረጃ አብልጣችሁ ሀላፊነት ልትወስዱ ትችላላችሁ ። ሙሉ በሙሉ የወያኔንም የሀላፊነት ድርሻ ደርባችሁ በሰላም ለመታገል ምርጫ ለመወዳደር ግን አታስቡ። ከናንተ በኩል ያለው ህጋዊና ሰላማዊ መሆኑን አረጋግጡ። ከዛ ውጪ ስልጣን ላይ ለመቆየት እገላለው አስራለው፤ ከህግ ውጪ እንቀሳቀሳለው እንደበፊቱ ካለ እድሉን ስጡት። እያደረገቻሁ እንዳላችሁት እናንተም የመሰዋትነቱ ቀማሾች እስከሆናችሁ ትግል ማለት ይህ ነው። አሸናፊ የሚያደርገንም ሚስጥሩ ያለው እዛ ላይ ነው። ውጤት እንዲያመጣ ከፈለጋችሁ ከአሁኑ ጠንካራ እንቅስቃሴ ጀምሩ። ከሁለት አመት በኋላ ምርጫው ከመደረጉ በፊት ወያኔ እራሱን እንዲገድል የሚያደርግ እንቅስቃሴ። የወያኔም የምርጫ እስትራተጂ በተቃራኒው እንደዛው ነው። በህግ ጠፍሮ፤ በማስፈራራት ተስፋ በማስቆረጥ መነሳሳት የሌለበት ፈዛዛ ምርጫ አካሂዶ ሸውዶ ማለፍ ነው።

## <u>ከቅንጅት ምርጫ በኋላ የነበረው የህዝብ ትግል ለምን ሞተ።</u>

እዚህም ጉዳይ ላይ ሁለት አይነት አመለካከት አለ። ወያኔ በሀይል እርምጃ እንደተቆጣጠረው ብቻ አርጎ የማቅረብና የሀይል እርምጃው ድርሻ አለው እንጂ የህዝቡን ለለውጥ መነሳሳት አላስቆመውም ትልቁ ምክንያት ትግሉ የቀዘቀዘው በመሪዎቹ መታሰር ትግሉ መሪ በማጣቱ ነው የሚል ነው። እኛ በሁለተኛው እንስማማለን መሪዎቹ ከታሰሩ በኋላ፤ ከሁለት ዙር ወያኔ ከአደረገው ጭፍጨፋ በሀያ ሺዎች ሰብስቦ ከአሰረ በኋላም ትግሉ ለስድስት ወር ቀጥሎ ነበር። ይህ ያለምንም መሪ ነበር ሲካሄድ የነበረው። ይህንን ስናየው ያኔም የዘመቻ ስራ ሁሌ ስህተት ስለማያጣው ነው እንጂ ብለሀት ነበረው። አሁንም የህዝብን ለለውጥ መነሳት የሀይል እርምጃ አያቆመውም ሌላ ስህተት ከአልሰራን ብለን እንድናምን ያደርገናል።

ወያኔ የሰራው ወንጀል ነው። ህዝብ ወንጀልን እንደጥንካሬ ቆጥሮ ከዚህ በኋላ ለትግል አይነሳም የሚለው ድምዳሜ ከባድ ነው። ምክንያት እስካለ፤ ሁኔታዎችን መፍጠር እስከቻልን ከህዝብ ጋር መገናኘት፤ እንዲታመንብን ልናደረገው እሰከቻልን ወያኔ ስልጣን ላይ እስካለ መቼም ለትግል ይነሳል። ምርጫ 97 ወያኔ ሲገድልና ሲያስር የመጀመርያው አይደለም ከዛም በፊት ብዙ ጊዜ በገፍ ሲገድል በገፍ ሲያስር ነበር።

## <u>እኛ ያለን እድል ምርጫውን እንደ አንድ መታገያ ማየት ነው።</u>

ምርጫ በሰላማዊ መንገድ ፕሮግራም አቅርቦ በዜጋው ምርጫ መንግስት ለመቀየር የሚደረግ ሂደት ነው። ያገራችን ሁኔታ ግን ይህን አይፈቅድም። ለዚህ አልታደልንም። የምርጫ ጥቅም ግን ይህ ብቻ አይደለም። ምርጫ ህዝብን ማስተማሪያ ነው፤ ምርጫ ከህዝብ ጋር መገናኛ ነው፤ የህዝብን ፍላጎት ማወቂያ ነው…. ምርጫ ትግልም ነው። ምርጫን አሁን በለው የኢትዮጵያ ሁኔታ ለመታገያ ማድረግ ይቻላል። ምርጫ 97 ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው።

እዚህ ላይ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ጥሩ እውቀት ያላቸው እናት አስተያየት እናስቀምጥ። ትንሽ እንድታውቋቸው ስለሳቸው አንዳንድ ነገሮች እናንሳ። ትምህርት የላቸውም እናት ናቸው። ወያኔ የገባ ሰሞን ኢትዮጵያ ውስጥ ከነበሩበት ቦታ ትጥቅ ከህዝብ አስፈትቶ በመኪና ጭኖ ሲወስድ መንገድ ላይ ቆመው ኡኡታቸውን አቀለጡት ጎረቤት ምን ተፈጠረ ብሎ ተሰብስቦ ምን ሆኑ ሲላቸው ምን ምን ሆንሽ ብላችሁ ትጠይቁኛላችሁ አገራችን ችግር ውስጥ የምትገባው ወያኔ አሸንፋን ስለገባች አይደለም ወንዱ ሁሉ መሳሪያውን ፈቶ ይህው መሳርያው ተጭኖ ሲሄድ እያያችሁ ብለው መለሱ።

ከምርጫ 97 በኋላ ተቃዋሚዎች ፓርላማ መግባት የለባቸውም ብለን እኛ ስንንጫጫ እሳቸው መግባት አለባቸው ነበር የሚሉት። እኛ የምርጫ መዘረፉን፤ የንጽሁናን ያላግባብ መጨፍጨፍ፤ ከውጪው አለም ይኖራል ብለን የነበረውን ድጋፍ ምክንያት ስናደርግ። እሳቸው ይህንን ሁሉ ትክክል ይሉንና እሳቸው ትግሉን ከማስቀጠል ህዝብ ጋር መድረስ ከመቻል አኳያ ነበር የሚያዩት። ፓርላማ ካልገቡ ይሆናል ያሉትም አንድም ጠብ ሳይል ነው የተፈጸመው። እኚህን እናት ዛሬም ተቃዋሚዎች የአሁኑ ምርጫ ላይ ቢሳተፉ ወይስ በአይሳተፉ ይሻላል ብለን ጠይቀናቸው ነበር።

ቀጥተኛ መልሳቸው ከአልተካፈሉ  ተሰብስበው ኪነት ያቋቁሙና ዘፈን ያውጡ ነበር። ለነገሩ ዛሬ በሀሳብ አንድ ነን። ለመሞገት ያህል። እማማ ወያኔ እንደባለፈው ኮሮጆ ይገለብጣል፤ ይገላል ያስራል፤ ህዝብ እንዳይሰበስቡ እየከለከለ ነው። መልሳቸው ይስረቃ ከፈለገም ይግደል ይሰር ይህ እሱን ይጭነቀው እንጂ እናንተ ምን ቤት ናችሁ። መስሏችሁ ነው እንጂ ያኔ ስለሰረቀ ስለገደለ ስላሰረ የተጎዳን እኛ ብቻ አይደለንም እኝ ልጆቻንን አተናል ያንገበግበኛል። ደግሞ ሁሌ እየገደሉ ህዝብን እየበደሉ መቀጠል አይቻልም። ይህው እናንተ ስትፍጨረጨሩ ያላችሁት ለዚህ አይደል። እኔኮ የናንተ ነገር ሰው ለአገሩ መሞት የለበትም መታሰር የለበትም እያላችሁ እንዴት ነው የምትታገሉት። ደግሞ ያኔ ሌላ ዛሬ ሌላ ጊዜ ነው። ዜናም አትሰሙም እንኳን ሌላ ገድሎ ለባለፈውም የአለም ፍርድ ቤት መለስ ይቀርባል እየተባለ አይደል። ስብሰባ ከለከለ እስከጭራሹ አይቻልም እስኪል አዲሳባ ስብሳባ አለ ብሎ ምክንያት ከአደረገ ወለጋ ላይ መጥራት ነዋ። እንደውም በሁሉም ከፍለ ሀገር ነው ለማድረግ መጠየቅ ያለባቸው። የሚል ነበር።

<u>የሚያሳስበው አንድ ሆነው መልሰው የህዝብን አመኔታ እንዴት ማግኘት ይችላሉ የሚለው ነው እንጂ እውነትም እማማ እንዳሉት ምን ሊሰሩ ነው ታዲያ። መካፈል የለባቸውም የሚሉት ክፍሎች ለመካፈል ያለውን ችግር እንዴት ያሸንፉታል፤ ምርጫውን አሸንፎስ ውጤቱን እንዴት መጠበቅ</u>

ይቻላል ነው የሚሉት እንጂ ምርጫ በአለመካፈል እንዴት ወያኔን ማስወገድ እንደሚቻል ወይ ትግሉ ተጠቃሚ እንደሚሆን አይደለም። ሌሎች ምርጫን የሚጠቀሙበትን ግልጋሎት ትተን እኛ ምርጫውን የትግል ስትራተጂ አድርገን ነው ማየት ያለብን። ከህዝብ ጋር መገናኛ፣ ትግሉን ማስቀጠያ ....ማድረግ ነው ያለብን።

እዚህ ጉዳይ ላይ የሚነሱ መከራከሪያዎች አንድ ምርጫውን ተቃዋሚ የሌለበት ማድረግ ለወያኔ ምክንያት ማሳጣት የሚል ነው። የምንታገለው ምክንያት ለማሳጣት ነው ለማስወገድ?። ለምክንያቱም አናሳጣውም ተቃዋሚዎች ይኖሩታል። ልደቱን ምን ብላችሁ ልታቆሙት ነው የጫሚሶንስ ቅንጅት። በአይመረጡም ተመጥኖ ይሰረቅላቸዋል ምን አልባት በአለፈው መለስ ለተቃዋሚው አሸንፈዋል ብሎ ከፈቀደው ቁጥርም የተሻለ መቀመጫ። ምንም ተቃዋሚስ በአይካፈል ወያኔ እጃቸውን ጠምዝዤ ምርጫ ውስጥ ላስገባቸው ወይ ነው የሚለው ይህም ምክንያት ነው።

ህጋዊነት ለማሳጣት ነው ሌላው አጢነን ከአሰብንበት ግን የወያኔ ጉዳይ ለኛ አንበሳ ምን ይበላል ተበድሮ ምን ይከፍላል ማን ጠይቆት ነው። በጉልበት ስልጣን ላይ ያለ ህጋዊ የማይሆን ቢሆን ኖሮ ከምርጫ 97 በኋላ እንኳ ህጋዊ አይደለህም ተቃዋሚውም ህዝብም ሌሎች አገራትም በአሉት ነበር። ከውጪ አገራት የሚያገኘውን ማንኛውንም ድጋፍ ለማሳጣት የሚሰማ ቢኖር አሁን ያለው ምክንያት በቂ ነበር። ለወደፊቱ ደግሞ ኮሮጆ ስለሚገለብጥ ምርጫ አልተካፈልንም አትርዱት ይሻላል። ይህው አሁንም ደግመን አሸንፈነው ኮሮጆ ገልብጦ ነው ስላጣኑ ላይ ያለው አትርዱት የሚለው ነው ምክንያታዊ?።

ትንሽ የሚመስለው መከራከርያ ህዝብ በድምጼ መንግስት እቀይራለው የሚል ተስፋ ውስጥ ገብቶ ወገቡን ጠበቅ አድርጎ ሌላ አማራጭ እንዳያይ ያደርጋል የሚልው ነው። የ97ቱ ምርጫ የተካሄደው ኢትዮጵያ ውስጥ ነው ምርጫውን ተከትሎ የሆነውም ሁሉ የሆነው እዛው ነው። ታዲያ ህዝቡ የሚቀጥለውን ምርጫ እንደትግል እንጂ አልጋ በአልጋ የሆነ መንግስት መቀየሪያ አድርጉ ከምን መነሻ ነው ሊያየው የሚችለው። ምርጫው ላይ የሚካፈሉ ተቃዋሚዎችም ደግመው ደጋግመው ማለት ያለባቸው ውጡና ምረጡን ድምጻችንን ግን ከመጀመርያውም ለመስረቅ እንዳይታሰብ ከተሞከረም ለማስመለስ አብረን የምንታገልበት ይሆናል ነው።

ተቃዋሚዎች አሁን በአለው ሁኔታ ምርጫ መግባታቸው ምን ጥቅም አለው? ነው እንጂ ምርጫ በአይገቡ ወይም ገብተው የ97 አይነት ምርጫ እንዲሆን ከአላደርጉ ትግሉ ላይ ምን ጉዳት አለው? ተብሎ እየታሰበ አይደለም። ቀጣዩን ምርጫ አስመልክቶ እዚህ ጉዳይ ስንጽፍ ሀሳብ ስንሰጥ አብረን ይህን ጉዳይ ለመመለስ ብንሞክር አቋም ላይ ጥራትን የፈጥራል እንላለን።

አሁንም እንለዋለን የሚያሳስበው አንድ ነገር ብቻ ነው። ተልፈስፍሰን ምርጫ ገብተን ማሸነፍ ብቻ አይደለም በዝረራ እንዳለፈው ከአላሸነፍነው። የህዝብን ተሳትፎ ከአለፈውም በበለጠ መፍጠር ከአልቻልን ። እስከጭራሹም ከአልተካፈልን ወያኔ ከሁለቱም ተጠቃሚ ነው። ለሌላ አምስት አመት ይቀጥላል። ይህ ምርጫው ላይ መካፈል ይሻላል አይሻልም ከሚለው መነሻ ነው። ወያኔ ስልጣኑ ላይ ለመቀጠል አይደለም ለሌላ አምስት አመት እስከምርጫውም የማያቆየው ነገሮች ሊኖሩ እንደሚችሉ እንገምታለን።

## ወያኔ ሰራቸው የሚባሉ ለሚቀጥለው ምርጫ ጥሩ ተወዳዳሪ ያደርገዋል የሚባሉት ነገሮች ምንድን ናቸው።

በነመለስ ጭንቅላት ታቅዶ ተሰራ የተባለው ኢህአዲግን ለሚቀጥለው ምርጫ አሸናፊ ተወዳድሪ ያደርገዋል የሚባለውን ለኢህዲግ እንደ ጥንካሬ የታየለትን ነገር እስቲ እንየው። ላለፉት ሶስት አራት አመታት ሰራተኛውን በስራው ዋስትና በማስፈራራት፣ ተማሪውን በትምህርት እድል ተመርቆ ሊኖረው በሚችል ስራ በማስፈራራት አባላትን ሲመዘግቡ ነበር። አምስት ይሁን ስድስት ሚሊየን ደርሰዋል። በዘጠና ሰባቱ ምርጫ ለተቃዋሚዎች ማሸነፍ ድርሻ ነበራቸው ያላቸውን መህበራትን ለመጫን አዳዲስ ህግ አውጥቷል። ስኬታችን ማለታቸው ስለማይቀር እንውሰድላቸው የተወሰነ የሚታይ መንገድና ህንጻ ተገንብቷል። በንግግርም በድርጊትም የህዝብን የትግል መንፈስ ለመስበር ህዝብን ምንም ማምጣት አልችልም ብሎ እንዲያምን ለማድረግ ሰርተዋል።

ኢህአዲግ አቅዶ ለሚቀጥለው ምርጫ ሰራቸው ከሚባሉት ውስጥ የትኛው ነው ታዲያ የህዝብን ድምጽ አስገኝቶለት ጥሩ ተወዳዳሪ ወይ አሸናፊ የሚያደርገው። በነጻ ምርጫ ለማሸነፍ ጥንካሬ ሆኖ ሊወሰድ ይችል የነበረው በፍላጎት አምነውበት ቢሆን አባላትን ማብዛቱ ነው። ተገደው በትእዛዝ ኢህአዲግ ሁኑ የተባሉት አይደለም ሌላ አሳምነው ለኢህአዲግ እንዲመርጥ ሊያደርጉ ግዜውን ነው የሚጠብቁት። ሌላው ቢቀር ሳይፈልጉ ከደሞዛቸው የምትቆነደደዋ ብር ታንገበግባቸዋለች። አንዳቸውም ድምጽ አይሰጡትም። ከውስጣቸው ጅላጅል ሆነው የሚሞክሩ ቢኖሩ እንኳ ሚስታቸውን ልጆቻቸውን ማሳመን አይችሉም።

የተወሰኑ የተሰሩ መንገዶችን ህንጻዎችን አሳይቶ የእድገት ቁንጮ ሆኖ ለመታየት መሞከሩም በአለፈውም ተሞክሮ አልሰራም አሁን እስከጭራሹ ህዝብ ሲሰማው የሚያመው ጉዳይ ነው። የህጉ ጋጋታ ማስፈራራቱ በነጻ ምርጫ ተወዳድሮ ለማሸነፍ ብቃት አለመኖርን አውቆ ኮሮጆ ለመገልበጥ እንዲመችና ተቃዋሚውን ለማሰናከል የተሰራ ነው። ኢህዲግ በምርጫ 97 እንዲሸነፍ ብቻ አይደለም ጥሩ የሚባል ተሸናፊ ያላደረጉት ምክንያቶች አንዳቸውም በዚህ አምስት አመት ውስጥ መልስ አልተሰጠባቸውም መፍትሄ አልተሰራባቸውም። አሁን ደግሞ ብዙ ሺ ምክንያቶች ተጨምረዋል። ኢህአዲግ በነጻ ምርጫ ኮሮጆ ሳይገለብጥ ማሸነፍ አይደለም ድርጅት ሆኖ መቀጠል አይችልም።

## ህዝብን ፈሪ በማድረግ የስልጣን እድሜን ማረዘም

ይህ ወያኔ ከባለፈው ምርጫ ተምሬ ሰራሁት የሚለው ኢህአዲግ ውስጥ ድንቅ ጭንቅላት አላቸው ተብሎ በምንስበከው በነመለስ እንደእቅድ ተወስዶ ሲለፋበት የነበረ ነው። ይህ እቅድ ለኢትዮጵያ ህዝብ ከአላቸው የኋላ ታሪካቸውም ከሚመሰከርው ንቀት ላይ የመነጨ ነው። <u>ህዝባችን እንዳሰቡት የመጨረሻ ፈሪ ቢሆን እንኳ ፍረሀቱ ለብቻው በሚስጥር ድምጽ በሚሰጥበት ድምጽ መስጫ ክፍል ውስጥም ይኖራል ወይ ብለው እንኳን አላሰቡም። እኛ ህዝባችን ያለፈውም ምርጫ የኋላ ታሪኩም አቅጣጫ አሲይዞ የሚመራው ከተገኘ ከመነሻውም ድምጹን ለመስረቅ እንዳያስቡ ማድረግ ይችላል። ለመስረቅ ከሞከሩም ድምጹን የማስመለስ አቅም አለው ነው የምንለው።</u>

ኢህአዲጎች ድርጅታቸውን እንኳ ማትረፍ የሚችሉት እነመለስን መሰዋት ቢያደርጉ ነበር። ከባለፈው ምርጫ ትምህርት ወስደው ታግለው የመጡ ተራ አባልቱ ለራሳቸውም በሂወት ለሌሉ ጓደኞቻቸውም ጭምር ሀላፊነት ተሰምቷቸው ወርደው ከአሉበት የሚከፈለው የድርጅቱ ሰራተኛነት እራሳቸውን አውጥተው የድርጅቱ በአለቤት  እራሳቸውን ቢያደርጉ ኖሮ ነበር።  ድርጅቱን እዚህ ችግር ውስጥ የከተቱን እጃቸው በንጽሁን ደም የተጨማለቀውን፣ በህዝብና በአገር ላይ በፈጸሙት ወንጀል የሚፈለጉትን ከውስጣቸው መንጥረው አውጥተው ለህግ ሰተው እውነተኛ ውስጣዊ ተሀድሶ አድርገው ቢሆን ኖሮ ነበር። ይህም ብቻም አይደለም ድርጅቱ በአገርና ህዝብ ላይ ለፈጸመው ወንጀል ጥፋተኝነትን ተቀብለው ይቅርታ ጠይቀውበት፣ በአዲስ አስተሳሳብ በአዲስ ፖሊሲ ብቅ ብለው ቢሆን ነበር ። ያኔ ይህን ድፍረትን የሚጠይቅ ትክክለኛ እርምጃ በመውሰዳቸው ህዝብ

ያደንቃል። መሰዋትነታቸውን አስተዋጾቸውን የሰሯትንም ትንሽም ብትሆን መልካም ነገር ፈልጎም ቦታ ይሰጠው ይጀምራል። ድርጅቱ እንደድርጅት ወንጀለኛ ሆኖ ከመጠየቅም ይተርፍ ነበር። ምናልባትም ኢህአዴግ ጥሩ ተወዳዳሪ ወይ ጥሩ ተሸናፊ ሊሆን ይችል ነበረ። ገንዘብ አላቸው፤ በድርጀት ስራ እውቀት አላቸው፤ በአስራ ሰበት አመት የስልጣን ዘመናቸው ላሸናፊነት የሚያበቁ ብዙ ጉዳዮችን በመምዘዝ የተካኑ ናቸው፤ የኛ ተቃዋሚዎች የሌላቸውን የመታገል ሳይሆን ያሸናፊነት ጭንቅላት አላቸው……በሌሎችም ብዙ ምክንያቶች ድርጅታቸውን ሂወት ኖሮት እንዲቆይ ማድረግ አገግመው ተመልሰውም ወደስልጣን ሊመጡም ይችሉ ነበር።

<u>ይህን አጠቃለን ስናየው እነመለስ ትክክለኛ ምርጫ አድርገው ለማሸነፍ ሳይሆን አዘናግተው ለሌላ አምስት አመት ለመቀጠል ነው። ምርጫ የሚባል ነገር የለም ማለት አይችሉም። ስለዚህ አንድ የባለፈውን አይነት የህዝብ ተነሳሽነት ያለበት ምርጫ እንዳይኖር ይታገላሉ። ሁለት እውነተኛ ተቃዋሚዎች ከምርጫው እራሳቸውን እንዲያገሉ የሚቻላቸውን ሁሉ ያደርጋሉ። ሶስት ተቃዋሚዎች ተባብረው እንዳይገጥሟቸው ልዩነታቸው ላይ ይሰራሉ። አራት ህዝብ በተቃዋሚዎች ላይ ግዴለሽ እንዲሆን ይሰራሉ። የመጨረሻ ግቡ ምርጫ ተካሂዶ ነበር እንዲባል ያህል ፌዛዛ ምርጫ አድርገው ሸውደው ማለፍ ነው።</u>

ከላይ በአነሳናቸው ጉዳዮች እንደምንስማማ ገምተን እንዴት አድርገን በምን እቅድ፤ ምን ብናደርግ ነው አራተኛውን አገራቀፋዊ ምርጫ ከ97ቱ ያላነሰ የህዝብ ተሳትፎ ያለበት የምናደርገው። ያውም ደግሞ ምርጫ አለ መባሉ ብቻ እንጂ ለምርጫ መሟላት የለባቸው ነገሮች በሌሉበት። ከባለፈውም በባሰ በሩ ሁሉ በተዘጋበት ይህን ምርጫ ውጤታማ የምናደርገው ለሚለው ጥያቄ መልስ መስጠት ብለሀት ማሰብ ማቀድ ያስፈልጋል። እኛ ይህ አካሄድ እነዚህ ችግሮች ያስወግዳል ወያኔ የፈራውን ምርጫ አይነት በዚህ መንገድ ብንሄድ ማድረግ እንችላለን ይሰራል ብለን ያመንበትን እቅድ እናስቀምጣለን።

## <u>ብርቱካናዊ ምርጫ እንዲሰራ ያልዘገየ ውሳኔ ያስፈልጋል።</u>

የተቃዋሚዎች አራተኛውን አገር አቀፋዊ ምርጫን አስመልክቶ ውሳኔ ያስፈልጋቸዋል። ለጥንካሬያቸው ለመጨረሻ ውጤቱ መልካምነት ውሳኔውን እንዴት መቼ ነው የሚያደርጉት የሚሉት ጉዳዮች ቀጥተኛ አስተዋጾ አለቸው። ሁለት አማራጮች አሉ አንድ አሁን እያደረጉ እንዳሉት ቅድመ ሁኔታዎች አስቀምጠው እነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች ከአልተሟሉ በምርጫ አንካፈልም በሚል አካሄድ ተጽኖ አድርጎ ቅድመ ሁኔታዎች ላይ እንዲወያይ ኢህአዴግ ላይ ተጽኖ ማድረግ። ሁለት በምርጫ እንካፈላለን ውሳኔ አሁኑኑ አስተላልፎ ለምርጫው በሙሉ ሀይል መስራት አሁኑኑ መጀመር። ቅድመ ሁኔታዎች እንዲሟሉ መታገል ነው። ሁለቱንም ምርጫዎች እንያቸው።

<u>ቅድመ ሁኔታዎች ካልተሟሉ ለምርጫ አንካፈልም።</u>

ይህ በተቃዋሚዎችም በወያኔም የቁርጥ የርግጡን ውሳኔ ጋር ነው መታየት ያለበት። ተቃዋሚዎች ያነሷቸውን ቅድመ ሁኔታዎች ወያኔ ለሚሟላት አይደለም እዚህ ጉዳይ ላይ ለመነጋገርም ፍቃድ ከአላሳየስ። የሚያደርገውም ይህንኑ ነው። የተቃዋሚዎች በውሳኔያቸው ጸንተው ሳይካፈሉ ይቀራሉ?። አይመስለንም። ቢያደርጉስ ወያኔ ምኑ ነው የሚጎዳው ትግሉስ የሚጠቀመው እንዴት ነው?።

የወያኔዎቹ የቁርጥ የመጨረሻ የርግጡን ውሳኔስ።፡ እነመለስ ስልጣን ብንለቅ ምሳችንን እናውቀዋለን ብለዋል። ከመቼውም ጊዜ በላይ አሁን እጃችንን ጠምዝዞ በግድ ከቤተመንግስት የሚያወጣን እስኪመጣ መልቀቅ አንችልም ብለው አምነዋል። አለመፈለግ አይደለም አንችልም ነው። ከመነሻው እዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ እራሳቸውን የሚከቱ እራስ ወዳዶች ስግብግቦች ብቻ ናቸው። በምንም ይሁን በምንም ያሉበት ሁኔታ ውስጥ አሉ። በነሱ ቦታ አርገን እራሳችንን ብናየው ምንስ ምርጫ አላቸው። ድፍረት የሚጠይቀውን ትክክል የሆነውን አርጎ እራስን ሰውቶ ለሎች የሚመች ነገርን መፍጠርን ለዛ ፍረሀታቸው በዝታ ስላለች በሀሳብ ደረጃ እንኳ በአይምሮቸውም የሚዞር አይደለም። ምክንያቶቹ ግን አሉ። ከትልቅ እንጀምርና የበለጠ ትርጉም ሊሰጣቸው ወደሚችለው ብንሄድ። አገር፣ ህዝብ፣ ዘር፣ ድርጅት፣ የትግል ጓዶች፣ ቤተሰብ፣ ልጅ፣ ለራስ የነግን ማሰብ ...ስለአንዱም ማሰብ ግን አይፈልጉም። ይህ ለነመለስ ምክር አይደለም። ተቃዋሚው እነመለስ ያሉበትን አጣብቂኝ፣ አስተሳሰባቸውን፣ ውሳኔያቸው ምን ላይ መሰረት ያደረገ ሊሆን እንደሚችል አጽኖት ሰቶ እንዲያየው ነው።

እነመለስ ትንሽ መለዘብ፣ ቀዳዳ መክፈት፣ የሚያመጣውን ጣጣ ከአለፈው ምርጫ አይተዋል። ተምረንበታልም ብለዋል። ከምርጫው በኋላ በሙሉ በሩን መስኮቱን በመቀርቀሪያ ሲቀረቅሩ፣ቀዳዳ ሲደፍኑ ነው ያሳለፉት። ከምርጫው በኋላ የተወሰኑ ውሳኔዎችቸውን፣ ስራዎቻቸው፣ ንግግሮቻቸው፣ የፕሮፓጋንዳው መሰረት፣ የአዳዲስ ህጎቹ ምክንያት፣ ሁሉ ነገር የሚጠቁመው ወደ አንድ አቅጣጫ ነው። በሂወት ወይ እስር ቤት ሳንገባ መኖር የምንችለው ስልጣን ላይ ከቆየን ብቻ ነው ብለው አምነዋል። ተቃዋሚዎች ያስቀመጧቸው ቅድመ ሆኔታዎች ላይ አይደራደሩም። ቢደራደሩም ለይስሙላ ነው እንጂ ከስምምነት በኋላም ቅድመሁኔታዎች ተፋጻሚ አይሆኑም።

<u>ጊዜ ሳይሰጡ አሁኑኑ ምራጫው ላይ እንካፈላለን ብሎ በግልጽ አቋም ውስዶ መሟላት ላለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች ለምርጫውም ቀጥተኛ ስራ፣ ትግል መጀመር።</u>

ተቃዋሚዎች ይህን በማድረጋቸው የወያኔን የሚቀጥለው ምርጫ ስትራተጂ በትልቁ መፈታተን ጀመሩ ነው እኛ የምንለው። ወያኔ ምርጫ የሚባል የለም እንዳይል መንገዱን አቶት ነው እንጂ ያለፈውን አይነት የዝረራ ሽንፈት፣ የህዝብ መነሳሳት መቋቋም እንደማይችል አውቆታል። ተቃዋሚዎችን ምርጫው ላይ እርግጠኛ ሆነው እንዳይወስኑ በአሳሪ ህግ ጋጋታ ተስፋ በማስቆረጥ፣ ተቃዋሚዎችን በማበሳጨት፣ በመተነኳከስ እርግጠኛ እንዳይሆኑ በማድረግ እንዲዘናጉ የማድረግ ብለሀት ነው የያዘው። በሌላ በኩል እነሱን አሳንሶ እያሳየ እሱ የተሻለ ተወዳዳሪ የተዘጋጀ እንደሆነ ፕሮፓጋንዳ በመስራት ከዛ እንደነገሩ የሆነ ፈዛዛ ምርጫ ለመስረቅም ብዙም የማይከብድ አድርጎ ሸውዶ ማለፍ ነው።

አባቶች ግርግር ለሌባ ያመቻል የሚሉት ለንደዚህ አይነቱን ጉዳይ ነው። እንድደለመድነው አፍንጫ ስር ደርሰን በዘመቻ ስራ ከመሯሯጥና ለሌቦች ከመቻቸት ዛሬ ውሳኔ ማሳለፍ ነው ለኛ የሚያዋጣን። በቀጥታ ምርጫው ላይ ለመስራት የሚኖረንን ጊዜ እናስበው። ምን ያህል የምርጫ ዘመቻ መስራት እንደምንችል። ምን ያህል ከህዝባችን ጋር ለመገናኘትና ለመምከር እድል እንደሚሰጠን። የህዝብም የተቃዋሚዎችም በአይምሮ መዘጋጀት፣ ህዝብ ከምርጫው ቀድሞ አሁን መስረቅ እንደማይችሉ ቀጥተኛ መልክት ለማስተላለፍ የሚኖረውን ጊዜ፣ ከላይ ያነሳናቸውን የአመለካከት ችግሮች ለማጥራት የምናገኘውን በቂ ጌዜ። ተቃዋሚው ከህዝብ ጋር መናበብ ለወሳኙ ትግል ልምምድ እያደረጉ መቆየት ጥቅሙ ተቆጥሮም አያልቅም። በሌላ በኩል ወያኔን ከምርጫው በፊት ቀድመን ወደ እውነተኛ በህሪው እንገፋዋለን ማሰር መግደል እንዲጀምር እናደርገዋለን። ይህ ሁኔታ ደግሞ ምርጫው ሳይደረግ እራሱን በራሱ እንዲገድል ነው የሚያደርገው።

## <u>መተባበር</u>

ብርቱካናዊ ምርጫ የምንፈልገውን ውጤት እንዲያመጣ ሌላ ተቃዋሚዎች ማድረግ ያለባቸው ተባብረው በአንድ መግጠም ነው። የኢትዮጵያን ሁኔታ ስናየው የማናሸንፈው ስላልቻልን ሳይሆን ስላልፈልግን ይመስላል። በተቃዋሚዎች በኩል። ለማሸነፍ ምን ማድረግ እንዳለብን እናውቃለን። ለምሳሌ ተበብረን ማሸነፍ እንደምንችል ሞክርነውም ተሳክቶ አይተነዋል። ከማሸነፍ በኋላ፤ ውርጂብኝ ከወረደብን በኋላ ሳንስማማ ስለቀረን መተባበር አያስፈልግም የሚል ድሜዳሜ ላይ በምን አይነት አስተሳሰብ ነው የሚደረሰው። ለዛውም ቁም ነገር በሌለው እስከዛሬም ለማንም በአልገባው ነገር ላይ ስለተጣሉ ስለሚጣሉ። የቅንጅት ተባብሮ ያለፈው ምርጫ ላይ መግባት እንዴት ሆኖ ነው ለመተባበር መጥፎ ምሳሌ ሊሆንስ የሚችለው። ልዩነታችሁን ማጥበብ ለቻላችሁት እና ለመተባበር እየሞከራችሁ ላላችሁት ይህ ሀላፊነት ከመሰማት ስለሆነ አምላክ ይባርካችሁ የምንደግፈው የምንፈልገው ጉዳይ ነው። ልዩነታችሁ ለበለጠባችሁ ለአሁኑ ልዩነታችሁን አስቆጥራችሁ ወያኔን በማሸነፍ ላይ ተባብሩ። ቅድሚያ ለሚሰጠው ቅድሚያ ስጡ ወያኔን ማሸነፍን ከአሳካችሁ በኋላ ተጣልታችሁ ሳይሆን ስላስቀመጣችሁት የአቋም ልዩነት በስምምነት ተለያይታችሁ አለን በምትሉት  ልዩነት ላይ በኋላ መወዳደር በህዝብ መፈረድም ትችላላችሁ። ስምምነቱን  እንደገና የሚታደስ አድርጎ የመጨረሻ ስምምነቱ የሚፈርስበትን አሳሪ የማይሆንበትንም የመጨረሻ ቀንም ማስቀመጥ ይቻላል እኮ።

ይህ አለን የምትሉት ልዩነት ለወያኔም አይታየውም ስለአገርና ስለህዝብ የሚባለው ቢቀር ሁላችሁንም በተራ በተራ እየቀጠቀጠ ነው። ህዝብም ለለውጥ ከአለው ፍላጎት ከመነሻውም ልዩነታችሁ አይገባውም እንዲገባው ፍላጎቱም ያለው አይመስልም። ህዝብ ወያኔን አስቀምጦ በናንተ ልዩነት ላይ ለመጫቃጨቅ ድምጽ ለመስጠት የደላው አይደለም ይህን በማድረግ ወያኔን እንጂ ማንኛችሁንም ድርጅቶች አላማችሁንም አሸናፊ ማድረግ እንደማይችልም ያውቀዋል። ይህን ደግሞ ከሌላ ዙር ስህተት በኋላ የምንማርበት እንደማይሆን እርግጠኞች ነን። ለሁሉም ጊዜ አለው ህዝብንና አገርን ለመታደግ ጊዜ አለው ፖለቲካ ለመስራትም ጊዜ አለው። ዞሮ ዞሮ ዘግይቶ ይመጣል ነው ፍራቻችን እንጂ የመተባበርን አስፈላጊነትን አገር ቤት ያሉት ተቃዋሚዎች ያጡታል ብለን አናስብም። ወይ እርስ በርሳቸው ተወዳድረው ለወያኔ ይመቹታል ብሎ ማሰብ ይከብደል።

አራተኛው አገራቀፋዊ ምርጫ ላይ ተቃዋሚዎች አልጋ በአልጋ የሆነ ሁኔታ አይገጥማቸውም። እገዛለው የሚለው ፓርቲ ሲፈጠር ጀምሮ ሁሉ ነገሩ እንግዳ ነው። ምርጫ አስፈጻሚው እንግዳ ነው። ምርጫ ታዛቢው ብቻ ሁሉም ነገር እንግዳ ነው። ለዚህ ለየት በአለ ሁኔታ ውስጥ ለሚደረግ ምርጫ የተለየ እንግዳ የሆነ እቅድ ያስፈልገዋል። እኛ በአራት ክፍል ከፍለን የኛን እናቀርባለን።

እንደገና እናነሳዋለን። አገራችንን ከዚህ በላይ ስህተት፤ ከዚህ በላይ መዘናጋትን፤ ከዚህ በላይ ያሉ አማራጮችን ሳይታዩ እንዲያልፉ ወይ ጊዜ የፈጠራቸውን አጋጣሚዎች ሳንጠቀም እንድናሳልፍ..... ሆና አይደለም ያለችን። ዛሬ ትክክል ለመሆና የናፈቅነውን ውጤት ለማምጣት መቅረብ ከአለበት ልንመረምረው ከሚገባ ብዙ አማራጭ ሀሳቦች እንደአንድ ተደርጎ እቅዳችን ይወሰድልን።

ለወደፊት ስራችን የህዝብ አስተያየት ጠቃሚ ነው። በዚህኛው ጽሁፍ በአነሳናቸው ቁምነገሮች ላይም  ከታች በምናስቀምጣቸው ጉዳዮች ላይ ህዝብ ቢወያይበት መልሳቸውን ቢያስብባቸው ጥሩ ነው ብለን እናምናለን።

1.የሚቀጥለው ምርጫ ላይ ሀ--መ ያስቀመጥናቸው ነገሮች ተዛማጅ ምልስ ሊኖራቸው ስለሚችል በአንድ ብናስቀምጣቸውም እያንዳንዳቸው በቂ መልስ የሚፈልጉ ችግሮች ናቸው እንዴት ነው ምርጫውን በኛ አሸናፊነት ለማጠናቃቅ መፍትሄ የምንፈልግላቸው። ለሁሉም ጥያቄዎች ግን ምርጫ ብቻ ይኖራል እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ ከወያኔ በኩል ምንም ፍላጎት የለም ተቃዋሚዎች ምርጫው ላይ መሳተፋቸው አይቀርም ብለን ወስደን ነው መልስ መፈለግ ያለብን። ከውጪ የሚገኝ ድጋፍንም ለአሁኑ እንተወው።

1.ሀ. ግድያ እስር ማስፈራራት
ለ. ነጻ ሜዲያ (ተቃዋሚው የሚሰማበት ሜዴያ)
ሐ. ነጻ ምርጫ አስፈጻሚ
መ.ሁሉም ምርጫ ጣቢያ መታዘብ የሚችል ታዛቢ

2. ህግ አስከባሪው እራሱን ገለልተኛ እንዲያደርግ ምን ማደረግ አለብን።

3. ድምጹን ከመስጠት በአለፈ የህዝብ ድርሻ ምን መሆን አለበት አገር ቤት ያለው በውጪ አገር የሚገኘው ብለን ከፍለን ማየት አለብን። ከግል አስተዋጾ ጀምረን የጋራ ወደሆነው አስተዋጾ አስበን።

4.የተቃዋሚ ድርጅቶች ድርሻ አገር ቤት ያሉት በውጪ ያሉት ሁለገብ ትግልንም ምርጫ ያደረጉትንም ጨምሮ

5. እንዴት ነው ከ97 ምርጫ በአልተናነሰ የህዝብ ተሳትፎ እንዲኖርበት የምናደርገው።

6. የህዝብ ድምጽ እንዳይሰረቅ ከመነሻው ምን ማድረግ እንችላለን። ከተሞከረስ እንዴት እናስቆመዋለን እናስመልሳለን።

7.ምን አይነት የቅስቀሳ መንገድ ነው በሚቀጥለው ምርጫ የሚያዋጣን።

8.ሊወሰዱ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች።

እነዚህንና ተመሳሳይ ጥያቄ እየፈጠርን መልስ መፈለግ አለብን። ችግር ከሆነ ጥያቄ ከሆነ መልስ መፍትሄ ሊኖረው ይገባል። የመወያየቱም አስፈላጊነቱ ብዙ ነን አንዳችን ጋር መልስ መፍትሄ ይኖራቸዋል። ትክክል ያልሆነ መልስም ትክክል የሆነውን መልስ ለማግኘት በማነጻጸርያነት ይረዳል። ትክክል የሆነውን መልስም ሊያጭር ይችላል። ሌላው የመወያየቱ ጥቅም የብዙዎች ጭንቅላት ሲሆን የመሳሳታችንን እድል ያጠበዋል።

ዳኮታ ጥናት ማእከል።
Dakotareserch@yahoo.com
04/22/09